በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን መስከረም 2 1 2012
Date
ቁጥር 1.0/48/12
Ref.No

**አስቸኳይ**

በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- የፀደቀ መመሪያ ይመለከታል፤

ከገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 14 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/1/2/20 በፃፈልን ደብዳቤ ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለውን የታክስ አስተዳደር አዋጅ በተሟላ የህግ ማዕቀፍ ተፈፃሚ ለማድረግ በአዋጁ ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የወጣውን የአስተዳደር ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 09/2011 የያዘ 9 ገፅ አባሪ ለተገቢው አፈጻጸም ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የተላከ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ሂሩት መብራቴ
የሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ

እንዲያውቁት፡-

- ለክብርት ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ አፕሬሽን ዘርፍ
- ለሕግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

ገቢዎች ሚኒስቴር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ለአዳማ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
አዳማ

ለሐዋሳ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
ሐዋሳ

ለባህርዳር ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
ባህርዳር

ለመቀሌ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
መቀሌ

ለድሬዳዋ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
ድሬዳዋ

ለጅማ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
ጅማ

ለኮምቦልቻ ገቢ.ዎች ሚ/ር ቅ/ጽ/ቤት
ኮምቦልቻ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No 7/ሕ/1/2/20
ቀን
Date 14/01/2012

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የገቢ ግብር አዋጅ በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ተፈፃሚ ለማድረግ በአዋጁ ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመ/ቤታችን እንዲወጡ ከሚጠበቁ 11 (አስራ አንድ) መመሪያዎች መካከል ከዚህ በፊት ከላክንላችሁ 8 (ስምንት) መመሪያዎች በተጨማሪ የአስተዳደር ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን ስለሆነ መመሪያው ከመስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter B/GT

# የገንዘብ ሚኒስቴር

# የአስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን

## መመሪያ

ገንዘብ ሚኒስቴር

ጳጉሜ 2011 ዓ.ም

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

# የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን
## መመሪያ ቁጥር 09/2011

**አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136ፊ/2/፣ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 09/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፣

1. "ያልተከፈለ ታክስ" ማለት በመክፈያ ጊዜ ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 32 በተደነገገው መሠረት የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ታክስ ነው፡፡
2. "አዋጅ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡
3. "ደንብ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 ነው፡፡
4. "ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለሥልጣን ነው፡፡
5. "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሠረት በሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን

## 4. ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች

1. ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች ተፈፃሚ የሚሆኑት በሕግ የመመዝገብ ግዴታ ላለባቸው እንዲሁም ሥራቸውን ሲያቆሙ ምዝገባው እንዲሠረዝ የማድረግ ግዴታ ለተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ነው፡፡

2. ለአዋጁ አንቀጽ 101/4/ አፈጻጸም በቂ ምክንያት ማለት ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ አደጋዎች ያጋጠመው እንደሆነ፣ ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴ በጽኑ ህመም ላይ የሚገኝ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ እንደሆነ ነው፡፡

## 5. ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት፣

1. ለአዋጁ አንቀጽ 102 አፈጻጸም በታክስ ሕጉ መሠረት መያዝ የነበረበት ሰነድ ማለት፡-

   ሀ. የገቢ ግብርን በሚመለከት ለደረጃ ሀ የትርፍና ኪሳራ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ ለደረጃ ለ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም እነዚህን መግለጫዎች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑ ሰነዶች

   ለ. የተጨማሪ እሴት ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በሚመለከት የግዢና ሽያጭ መዝገብና ታክሱን ለማስላት የሚረዱ ደጋፊ ሰነዶች፣

   ሐ. የኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት ታክሱን ለማስላት የሚያግዙ የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች፣

2. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንደያዘ የሚቆጠረው ያቀረበው ሰነድ ስለመዝገብ አያያዝ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የቀረበ እና አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች እንዲያቀርብ ባለሥልጣኑ ሲጠይቀው ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 3

3. ለአዋጁ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና (ለ) አፈጻጸም የታክስ ዘመን ማለት :-

ሀ. ለገቢ ግብር ማስታወቂያ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፈነው የአንድ ዓመት ጊዜ፣

ለ. ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንደታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን አንድ ወር ወይም ሶስት ወር፣

ሐ. ለተርን ኦቨር ታክስ የደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች እንደ ታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን አንድ ወር ወይም ሶስት ወር፣ ለደረጃ ለ ታክስ ከፋዮች ሶስት ወር ነው፡፡

መ. ለኤክሳይዝ ታክስ ምርት አንድ ወር ነው፡፡

## 6. <u>ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት</u>

ለአዋጁ አንቀጽ 103/3/ አፈጻጸም "የገንዘብ ጥቅም" ማለት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው የራሱ ያልሆነውን መለያ ቁጥር በመጠቀም በሰራው ስራ ካገኘው የሽያጭ ገቢ ገቢውን ለማግኘት ያወጣው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ያለው ልዩነት ነው፡፡

## 7. <u>የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት</u>

1. የታክስ ማስታወቂያን ዘግይቶ በማቅረብ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 2/35 መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው በሚገባ፡-

ሀ) በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፣

ለ) በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ታክስ በሚመለከት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ሐ) በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ፣

መ) ወደ አገር በገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣

ሠ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ረ) በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ እና፣

ሰ) በአዋጁ መሠረት በታክስ ከፋዩ መቅረብ የነበረበት የታክስ ማስታወቂያ ላይ ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 3

2. የአዋጁ አንቀጽ 104 (1) ለተጣለው ቅጣት "የታክስ ጊዜ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(38) በተሰጠው ትርጉም መሠረት ሆኖ የቅጣቱ አወሳሰን ፡-

ሀ) ለገቢ ግብር አዋጅ በዓመት፣

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንደታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን በየወሩ ወይም በየሶስት ወሩ፣

ሐ) የደረጃ ሀ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ እንደታክስ ከፋዩ የግይት መጠን ለእያንዳንዱ በወር ወይም በሶስት ወር፣

መ) ለኤክሳይዝ ታክስ በወር

ሠ) ለደረጃ ለ ለተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ በየሶስት ወሩ፣

ረ) ከተከፋይ ሂሳብ ተቀንዶ የተከፈለን ሳይጨምር የሰንጠረዥ መ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 104 መሠረት የሚሠላ ይሆናል፣

3. በአዋጁ አንቀጽ 104 መሠረት የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው የዘገየው የታክስ ማስታወቂያ እንደ አንድ ጥፋት ተቆጥሮ አንድ ቅጣት ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

4. ይህ አንቀጽ በደረጃ ሐ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

8. <u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ግብር ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት</u>

1. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ባለመክፈል በአዋጁ አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረው ገንዘብ በታክስ መክፈያ ጊዜ ባለመክፈሉ ይሆናል፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 106(2) በተደነገገው መሠረት ግብር ቀንሶ ገቢ ያላደረገ፡-

ሀ) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ እና

ለ) ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ዋና ሂሳብ ሹም የሌለ እንደሆነ ታክስ ቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ በእያንዳንዱ የታክስ መክፈያ ጊዜ ተቀንሶ ገቢ ላልተደረገ ግብር እያንዳንዳቸው ብር 2000 ቅጣት ይከፍላሉ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ቢኖርም አንድ ሰው ከአንድ በላይ ኃላፊነቶች ደርቦ የሚሠራ ከሆነ የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው እንደ አንድ ኃላፊ ብቻ ይሆናል፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

4. በአዋጁ አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 3 የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92(3) ተፈጻሚ በሚደረግባቸው ገገር እና አቅራቢ ላይ ነው፡፡

## 9. ደረሰኝ ባለመስጠት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ደረሰኝ በመስጠት የሚጣል ቅጣት

1. አዋጁ አንቀጽ 108 መሠረት ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥው ባልሰጠው ለእያንዳንዱ ግብይት ብር 50,000 ይቀጣል፡፡ ይህ ድንጋጌ ማንዋል ደረሰኝ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይ ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለሚቀነስ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 10. ታክስ አሳንሶ በማስታወቅ የሚጣል ቅጣት

በአዋጁ አንቀጽ 109 መሠረት የጣለው ቅጣት ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ለሁለተኛ ጊዜ፣ ለሶስተኛ ጊዜ፣ እና ከዚያ በላይ የተፈፀመ በሚሆንበት ጊዜ የተለያየ ሲሆን የጥፋቱ መጠን የሚቆጠረው አዋጁ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለየታክስ ዓይነቱ ተለያይቶ እና የታክስ ስሌት ውሳኔው በአንድ ጊዜ የተወሰነ ቢሆንም ጥፋት በተገኘባቸው የታክስ ማስታወቂያዎች ብዛት ነው፡፡

## 11. ታክስን በመሸሽ የሚጣል ቅጣት

በአንቀጽ 110 የተጣለው ቅጣት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 78 እስከ 80 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 60 ታክስን መሸሽን ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በመተላለፉ በተፈፀሙ ድርጊቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 12 የታክስ ማስታወቂያና መክፈያ ጊዜ

1. አንድ ታክስ ከፋይ ታክስ ያስታወቀበት እና የከፈለበት ጊዜ የተለያየ ከሆነ ታክስ ባለማስታወቅ እና ታክስ ባለመክፈል የሚጣል ቅጣት የዘገየውን ጊዜ መሠረት በማድረግ ተለያይቶ መወሰን አለበት፡፡

2. ታክስ ከፋይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ወደ ባለሥልጣኑ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገ ቢሆንም የታክስ ማስታወቂያ በወቅቱ ሳያቀርብ ያዘገየ ከሆነ ቅጣት የሚጣልበት በአዋጁ አንቀጽ 104 ድንጋጌ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ባለማቅረብ ወይም ዘግይቶ በማቅረብ ብቻ ይሆናል፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## 13. ታክስ ከተወሰነ በኋላ ባልተከፈለው ታክስ ላይ የሚወሰን ቅጣት

1. አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ በተሰጠው በ30 ቀን ውስጥ ታክሱን ከከፈለ በአዋጁ አንቀጽ 37(8) በተደነገገመ መሠረት ወለድ የማይታሰብበት ሲሆን፣ በተመሳሳይ የአስተዳደራዊ ቅጣትም ተፈጻሚ አይደረግበትም፡፡

2. ታክስ ከፋዩ በቅሬታ እና በይግባኝ በቆየበት ጊዜ ባልተከፈለ ታክስ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡ ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በቅሬታ እና በይግባኙ ውሳኔ መሠረት በግብር ከፋይ ላይ በሚፀናው የግብር መጠን ልክ ይሆናል፡፡

## 14. መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት

ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 65 መሠረት በጽሁፍ ማስታወቂያ ሲጠይቀው በጽሁፍ በማስታወቂያው በተጠቀሰው ቦታ እና ጊዜ የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በአዋጁ አንቀጽ 114(7) በተደነገገው መሠረት 5000 ብር ቅጣት ይጣልበታል፡፡

## 15. ስለቅጣት አወሳሰን

1. ባለሥልጣኑ የሚወስነው አስተዳደራዊ ቅጣት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

2. አንድ ድርጊት መፈጸም ወይም ያለመፈጸም የሚያስከትለው ቅጣት በአንድ ታክስ ብቻ ያልተወሰነ ሲሆን እያንዳንዱ ቅጣት ለየብቻ ከተወሰነ በኋላ ሁሉም ቅጣቶች ተጠቃለው ይጣላሉ፡፡ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነወ በተለያዩ የታክስ ዓይነቶች ለሚፈጸሙ የሚከተሉት ጥፋቶች ብቻ ነው፡፡

   ሀ) ሰነድ ባለመያዝ፣
   ለ.) ታክስ በጊዜው ባለማስታወቅ፣
   ሐ) ታክስ ዘግይቶ መክፈል፣
   መ) ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ፣
   ሠ) ታክስን መሸሽ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው አንድን ታክስ በሚመለከት ታክስ ከፋዩ የተለያዩ ድንጋጌዎች የጣሰ በሚሆንበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. የተሻሩ አዋጆች ተፈጻሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሂደት ውሳኔ ሳያገኙ የቆዩ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ

### 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ መስከረም 14 ቀን 2011 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2